# የኢትዮጵያ ሕዝብ፣ አገር-ወዳድና ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች እና ኢሕአዴግ፤ ከዚኽ ወዴት?

*ከአያል ሰው ደሴ፤- የግል አስተያየት*

***ክፍል አራት****(ከክፍል ሦስት የቀጠለ)*

ምንም እንኳ ሕወሓት በ"ግራ-ቀመስ" የብሔረሰበኝነት የፖለቲካ ፍልሥፍና ለትግራይ ብቻ እቆማለሁ ብሎ የተመሠረተና የታገለ ድርጅት መሆኑ ቢታወቅም በታሪክ አጋጣሚ በኢሕአዴግ ስም አገራዊ ሥልጣን ሲይዝ የተከተለውና የሚመራበት ዋነኛ የፖለቲካ ፍልሥፍናው አብዮታዊ ዴሞክራሲ እና የአገራዊ አስተዳደር መርኍ ደግሞ ኢትዮጵያን "ብሔር፣ ብሔረሰብና ሕዝቦች" በሚል ሕዝብን ቋንቋንና ጎሣን መሠረት ባደረገ አወቃቀር የከፋፈለ እንደሆነ አይተናል፡፡ እነኝኽ ጣምራ እምነቶች (ፖለቲካዊ ብሔረሰበኝነትና አብዮታዊ ዴሞክራሲ) ላይ መሠረቱን የጣለ ድርጅት እንደ ኢትዮጵያ ላለ የብዙ ቋንቋዎችና ብሔረሰቦች ባለ-ፀጋ ለሆነ አገር የሕዝብ አመኔታንና ሉዓላዊነትንም ሆነ የግለሰብ ነፃነትን፣ የዜጎች እኩልነትንም ሆነ የሕግ የበላይነትን፣ ከአድልዖ ነፃ የሆነ አስተዳደርንም ሆነ ፍትኅን፣ አስተማማኝ አገራዊ አንድነትንም ሆነ ሁሉም እኩል ተጠቃሚ የሚሆንበት አስተማማኝ ብልፅግናና እድገትን፣ ወዘተ.. የሚያስገኝ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት እንዲሰፍን ለማድረግ በእጅጉ እንደሚገደው የታወቀ ነው፡፡

በእርግጥ የአገዛዙ መሪዎችና የፖለቲካ ሓዋርያዎቻቸው (ካድሬዎቻቸው) እንደ ቻይና የመሣሰሉትን አገሮች እንደ ምሳሌ በመጠቃቀስ የሚከተሉትን ፍልሥፍናና አመራር ትክክለኛነትና አልፎም እንከን-የለሽነት ሊያሳምኑ መቃጣታቸው እየታዬ ነው፡፡ ሆኖም ቻይናም ሆነች ሌሎቹ አገዛዙ በምሳሌነት ሊያቀርባቸው የሚከጅል አገሮች ለአንድ የተወሰነ የአገሪቱ ክፍል ብቻ ቆሚያለሁ ባለና በታገለ አልፎም እንደ ሁኔታው ለመገንጠልም በሚዳዳ ድርጅት የሚመሩም ሆነ አስተዳደራቸውም የአገራቸውን ሕዝብ ቋንቋንና ብሔረሰበኝነትን ብቻ በመለኪያነት ባስቀመጠና መሠረት ባደረገ ዘይቤ በከፋፈለ የልዩነት አጥር-አጣሪ እና ነፃነት-ገዳቢ አወቃቀርን የተከተሉ ሣይሆን፤ ዜጎች እንደ አንድ አገር ሕዝብ አንድ ዜግነት ያላቸውና የሁሉም የአገሪቱ ልዩ ልዩ ብሔረሰብ ባህሎችና ቋንቋዎች እንዲያብቡና እንዲዳብሩ ከማበረታታት ውጭ ፖለቲካዊ ብሔረሰበኝነትን (ጎሠኝነትን) ከአገር እስከ-መገንጠል የማያበረታቱና የማይቀበሉ መሆናቸው ሊታወቅ ይገባል፡፡ ያም በመሆኑ እንደ ኢትዮጵያ የብዙ ቋንቋዎች ተናጋሪ ባለ-ፀጋና ኍራማይሌ ባህሎች ባለ-ዕድል በሆነችው ሕንድ ረሃብንና ድህነትን አስወግዶ ልማትና እድገትን በአጭር ጊዜ ለማምጣት የተደረገው አገር-አቀፍ ጥረት እየተሣካ የመጣው ትርጉም በሌለውና በተቃርኖ በተሞላ በልዩነት ላይ የተመሠረተ የዋለለ አንድነት ላይ በቆመ እምነት ሣይሆን፣ ልዩነትን በአንድነት ላይ በመሠረተ የጠና አስተሳሰብ የአገሪቱን ዜጎች እኩል በሚያሣትፍ ዴሞክራሲያዊ አስተዳደር እንደሆነ ሁሉ፤ እንደ ቻይና ዓይነት ደግሞ ፖለቲካው በአጠቃላይ የግራ ርዕዮትን በግልፅ ሣይለቅና መዋቅሩን ሳይተው ወደ-ግራ አጮልቆ እያየ ወደ-ቀኝ አፍጥጦ በጥድፊያ የሚገሠግሰውና ልማትን እያጧጧፈ ያለው የአገሪቱን (የቻይናን) ሕዝብ በትኖ ለመሰብሰብ በሚያስብ በልዩነት ላይ በተመሠረተ ቀዶ ለመስፋት በሚከጅል ተላላ መንግሥታዊ አወቃቀርን በመከተል ሣይሆን የሕዝብንና የአገርን አንድነት በቀናኢነት በሚያይ፣ ለተወሰነ የቻይና ክፍል የቆመ ሣይሆን በአንድ ወቅት ሕዝብን በመደብ ቢከፍልም የሁሉንም የቻይና ዜጎች እንደ አንድ አገር ዜጎች በተቀበለና እምነቱም ለሁሉም እኩልነትን ለማስገኘት በተቋቋመና በታገለ ብሔራዊ ድርጅት መሆኑ ሊታወቅ ይገባል፡፡

ስለሆነም በአገራችን ያለውን የፖለቲካ ሁኔታ ለመቀየር የሚታገለው ለአዎንታዊ ለውጥ የቆመው ወገን የሚከተለው የፖለቲካ ፍልሥፍናም ሆነ አደረጃጀቱ ኢሕአዴግ የቆመበትንና የሚከተለውን ዓይነት ቅኝት የያዘ ከሆነ የሚያደርገው ትግል ለአዲስ ቀንና ለተሻለ ብሩኅ ተስፋ ሣይሆን ለተመሣሣይ ውጤት ስለሚሆን ጥረቱ ከንቱ ነው፡፡ ያ ከሆነ ደግሞ ችግሩ ያለው ከድርጅቱ ከኢሕአዴግና ከሰዎቹ (ከመሪዎቹ) እንጂ ከሚከተሉትና ከቆሙበት መሠረታዊ ፍልሥፍና አይደለም ማለት ነው፡፡ በዚያ አስተሳሰብና ስሊት

*የሚመራ ትግል ደግሞ የጨዋታ ሕጉን ሣይሆን ተጫዋቾቹን በመቀየር ላይ ብቻ ያተኮረ ስለሚሆን ግቡን የመሣት ዕድሉን ያሠፋ ትግል ከመሆን እንደማያልፍ ጥርጥር አይኖረውም፡፡*

*ለአዎንታዊ ለውጥ በቆምን ሕዝባዊ ኃይሎች በኩል ለጊዜው ግር የሚል ቢመስልም ከሁሉ በፊት ጠይቀን በአሳማኝ ሁኔታ መመለስ ያለብን የምር ጥያቄዎች አሉ፡፡ ኢሕአዴግ ሊለወጥ ወይም ሊሻሻል የሚችል ነው ወይንስ ጨርሶ ሊወገድ የሚገባው ድርጅት ነው? ለምንና እንዴት? ለመሆኑ በአሁኑ ጊዜ ኢሕአዴግ መቀየር አለበት የምንልበት ዋነኛ ምክንያት/ምክንያቶች ምንድን ነው/ናቸው? ለአዎንታዊ ለውጥ የቆመው አገር-ወዳድና ሕዝባዊ (ዴሞክራት) ወገን ከኢሕአዴግ ጋር ያለው ችግር ከመሪዎቹ ነው? ከድርጅቱ ጋር ነው? ወይስ ከያዙትና ከሚመሩበት ፍልሥፍና ነው? በአገሪቱ ለውጥ እንዲመጣ የሚታገለው አገር-ወዳድና ሕዝባዊ (ዴሞክራት) ክፍል እስካሁን የሚከተለው የፖለቲካ ፍልሥፍና፣ አደረጃጀት፣ የትግል ስልትና የግብ ትልም (ስትራቴጂ) ኢሕአዴግ ከያዘውና መለወጥ አለበት የምንለውን ይመጥናል ወይ? ካልሆነስ ምን መደረግ አለበት? ለእነኝኽ ጥያቄዎች አግባባዊና ቀጥተኛ ምላሽ መስጠቱ የተያያዝነው ሕዝባዊ ትግል ውጤት በማምጣትና ባለማምጣቱ ላይ ወሳኝነት ይኖረዋል የሚል እምነት አለኝ፡፡*

*በአጠቃላይ በአሉታዊነት ጎኑ ኢሕአዴግ አውራ ድርጅቱ ሕወሓት ሥልጣን ከመያዙ በፊት ከነበረውና ከታገለበት አቋሙ፣ ከመሠረታዊ የፖለቲካ ፍልሥፍናውና እሠራዋለሁ ብሎ ይፋ ከለፈፈው ውጭ የሠራው የለም ማለት ይቻላል፡፡ ሆኖም "ሊተናኮል የመጣ ተደብቆ፣ መንተፍረቱን ሄደ አስታርቆ"* የተባለውን ዓይነት ምሣሌአዊ አባባል ባይሆንም በአንድ በኩል ይኽ ድርጅት ይዞት በተነሣው ጠባብ እምነቱና ሥልጣን ከያዘ ጀምሮ በሂደት ፈለገም አልፈለገ የያዘው አገራዊ ሥልጣን በሚያሳድርበት ጫና ምክንያት ማስተናገድና መሥራት የሚገደድበትንና የሠራቸው ተግባራትም ሆኑ ወደ-ፊት ሊሠራቸው የሚችል እቅዶች መኻል ያለውን በተቃርኖ የተሞላ አካሄድ በተገቢ ማገናዘብና ያም በትግሉ ይዞታና ሂደት ላይ የሚያስከትለውን ተፅዕኖ በቅጡ መገምገሙ በጣም አስፈላጊ ይሆናል፡፡*

*ሕወሓት በኢሕአዴግ ስም አገራዊ ሥልጣን ሲይዝ የነበረውን እምነትና አቋም ሙሉ በሙሉ ይዞ በሥልጣን ላይ መቆየት እንደማይችል ሁሉ በአንፃሩም ያን እምነትና አቋም በሙሉና በአንድ ጊዜ እርግፍ አድርጎ መተው እንደማይችል የታወቀ ነው፡፡ እዚኽ ላይ በቅጡ ግንዛቤ ሊወሰድበት የሚገባውና ከፍ ሲል የገለጽኩት አስተሳሰብ የተወላገደ ትርጉም ከመስጠቱ በፊት ኢሕአዴግ አገራዊ መንግሥታዊ ሥልጣን ከያዘ በኋላ ያደረገው ግዴታዊ ውስጣዊ መሸጋሸግ በሦስት ተያያዥ ምክንያቶች እንደሆነ ግልፅ ማድረጉ አስፈላጊ ይሆናል፡፡*

*አንደኛ ኢሕአዴግ በአገራዊ ሥልጣን ላይ ሲቆይ አገር-አቀፍ አስተሳሰብ፣ እምነትንና ምላሽን የሚጠይቁ እንደ አገር መከላከያ-ነክ ጉዳዮች፣ እንደ ግድቦች፣ የነዳጅና ሌሎች የኃይል ማመንጫ እቅዶችና በብሐራዊ ደረጃ ብቻ የሚሠሩ የተለዩ የግንባታ ተግባራትና ተቋማት፣ ለነዚኽ ሁሉ አስፈላጊ የሆኑ የውጭ ግንኙነቶችን፣ ወዘተ የመሣሰሉ አገር-አቀፍ ጉዳዮችን ሁል-ጊዜና ምን-ጊዜም አውራው ድርጅት ሕወሓት ሲነሣ ይዞት በነበረው እምነትና አስተሳሰብ ሊያስተናግድ ጨርሶ ስለማይቻለው የግድ አገራዊ በሆነ ይዞታ መሥራት ይገደዳል፡፡ ይሁንናም ዞሮ ዞሮ በሁለት ተቃራኒ ጥቅሞችና አስተሳሰቦች ተወጥሮ የተያዘ ኃይል እንደመሆኑ፣ በአሁኑ ጊዜ አገዛዙ እንዳመቸው ከአንዱ ወደ-አንዱ እየዘለለም ሆነ እያምታታ ለመቀጠል መሞከሩ የግድ ይሆናል፡፡*

*ሁለተኛ አገዛዙ እነዚኽን "አገር-አቀፍ አስተሳሰብ፣ እምነትንና ምላሽን የሚጠይቁ" አገር-አቀፍ ጉዳዮችን ማስተናገድ በቀጠለ ቁጥር የአሰላለፍና የይዞታ ለውጥ ማድረግን የሚያስገድዱ ቀጥተኛ ጫናዎችን መፍጠራቸውና ማሳደራቸው የማይቀር ነው፡፡ ምንም እንኳን እነዚኽን ጉዳዮች ሁሉ የኢሕአዴግ መሪዎች ለብሔራዊ ጥቅም በሚውሉበት መልክ ይሠሯቸዋል ወይም ይፈፅሟቸዋል ብሎ መጠበቅ ባይቻልም፤ ቁም-ነገሩ መነሻየ ላይ እንዳልኩት በተለይም ከምርጫ-ሁለት-ሽህ-ሁለት ወዲኽ አገዛዙ ለጊዜው ፖለቲካዊ*

*(*አንድ ጉልበት የተሰማው ሰው ለመደብደብና ለመበቀል የገባበት ቤት በቀረበለት ያልጠበቀው ትንትና የተሞላበት ግብዣ ምክንያት ጨርሶ ያላሰበውን የተኳረፉ ባልና ሚስትን አስታርቆ እንደተመለሰ ይነገራል፡፡)*

ዋጋነትም ቢሆን ለዚኽ በለጥ ያለ ትኩረት ሊሰጠው ሁኔታው የግድ ስለሚል፣ ያም ደግሞ ሕዝብ በተለይም አዲስ የተሰበኩ አባሎቻቸው፣ ደጋፊዎቻቸውና ተከታዮቻቸው ከአገዛዙ ብዙ መጠበቃቸው የግድ ነውና፣ ይኽንን ጥበቃ ለማሟላት ስለሚገደረደሩ የአገዛዙ መሪዎች ፈለጉም አልፈለጉ በአካሄዳቸውና በአመራራቸው አጠቃላይ ሁኔታ ላይ የሚያሳድረው ጫና ቀላል አይሆንም። ከእነዚኽ "ብሔራዊ ጉዳዮች" መካከል አንዳንዶቹ፣ በተለይ ሥራ ላይ የዋሉና የተጀመሩ፣ የአገዛዙ መሪዎች ቢፈልጉም እንኳን ሊቀለብሷቸው ስለማይችሉ በጉዳዩ ላይ ለመግፋት ይገደዳሉ። ይኽ ጫና ደግሞ አሁን በሥልጣን ቁንጮ ላይ ካሉት በበለጠ በቀጣዮቹ ተተኪዎቻቸው ላይ (በሥልጣን መቆየት ዕድል ካላቸው) ከበድ የሚል እንደሚሆን መገመት ቀላል ነው። ድኅረ-ምርጫ ሁለት-ሽህ-ሁለት ያለው ኢሕአዴግ አገራዊ ሆኖ መቅረብና መታዬት አስፈላጊም ግዴታም እየሆነ ስለሚመጣበት በውስጡ ያሉ ድርጅቶች የተፈጠሩበትና ይዘውት የሚንገታገቱበት ክልል-ተኮር አመለካከት ቀስ-በቀስ እየኮሰመነና አንፃራዊ በሆነ መልኩ አገራዊ (ብሔራዊ) አዝማሚያ የመያዝ ግፊቱ እያየለ ስለሚሄድ የአሁኑ የኢሕአዴግ መሪዎች መረጡትም አልመረጡት ቀጣይ ዙር ኢሕአዴጎች አሁን ያለውን የአንድ ፓርቲ አምባ-ገነንነት ጅማሮ አጠናክረው የሚቀጥሉበት የመሆን ዕድሉ ሠፊ ነው። ያ ማለት ግን ለለውጥ የቆመው ሕዝባዊ ኃይል አዲስ አንድ-ወጥ አደረጃጀትን የያዘ አስገዳጅነት ያለው ሚና ካልታከለበት ኢሕአዴግአዊ የፖለቲካ ብሔረሰበኝነት ጠባብ አመለካከት ይከስማል ማለትም ሆነ ኢሕአዴግ አንድ ፓርቲ እየሆነ መምጣቱ ጠቃሚ ነው ማለት አይደለም።

ሦስተኛ የአገዛዙ መሪዎች እየተናነቃቸውም ይሁን እየለመዱት እነዚኽን ማድረግ ካልቻሉ በሥልጣን ላይ ለመቆየት አይቻላቸውም። ስለሆነም አገር-አቀፍ ይዞታና ቅኝት የሚያንፀባርቅ ካባ መደረባቸውና በዚያም ከመቀጠል ውጭ ምርጫ ላይኖራቸው ይችላል።

ጥያቄው እንግዲህ የአገዛዙ መሪዎች ድርጅታቸው እነዚኽን ሁለት አብረው የማይሄዱና ተቃራኒ እምነቶች ማለትም መሠረታዊ የፖለቲካ እምነትና ፍልሥፍናቸው የሆኑትን ፖለቲካዊ ብሔረሰበኝነትና የአብዮታዊ ዴሞክራሰን ከዚኽ ሁኔታው እንዲከተሉ የግድ ከሚጠይቅ አገራዊ አስተሳሰብና ምሪትን ከሚሻ "አዲስ እምነት" ጋር አጣጥሞ አለያም ደግሞ እንዲሁ አንፈራጦ ማስኬድ ይቻላቸዋል ወይ? የሚለው ይሆናል። የኢሕአዴግ መሪዎች በአንድ በኩል የተነሱበትንና የቆሙበትን መሠረት በጎላ መልኩ ብዙ ሳያናጉ፣ በሌላ በኩል መንግሥታዊ ሥልጣናቸውን ለማቆየት አገር-አቀፍ እይታዎችን ሊያንፀባርቁ የሚችሉና ለሕዝብ የገቡትን ቃል ለመጠበቅና ሕዝብም ይደረግልኛል ብሎ የሚጠብቀውን ለማሟላት አንፈራጦ የመሄድ ጥረት ማድረጋቸው የሚጠበቅ ቢሆንም ሁለቱን ተቃራኒ አስተሳሰቦች እስከ-ወዲያኛው አቻችሎ መቀጠል ጨርሶ ስለማይቻላቸው አንዱ በሌላው ላይ ገዥነት ሊኖረው የግድ ይላል። በምርጫ ሁለት-ሽህ-ሁለት ያረጋገጡትን አገሪቱን ወደ-አንድ ፓርቲ አገዛዝ የመቀየር ግልፅ አቅጣጫ ሊቀለብሱት አይችሉም። ይኽ በራሱ በድርጅቱ በኢሕአዴግ የውስጥ አሠራርና ይዞታ ላይ አይቀሬ ጫና አለው። ስለሆነም ምርጫቸው በሥልጣን መቆየት እስከሆነ ድረስ ወደዱም ጠሉ የግድ ይኽንን ተቃርኖ ለመፍታት ፊት ለፊት ከመላተምና በአንድ ጊዜ አንዱን ከሌላው ለማስቀደም ከመሞከር ውጭ ሌላ አማራጭ አይኖራቸውም። አንዱ በሌላው ላይ ገዥነት መኖሩ የግድ ከሆነ ደግሞ ሌላው ቢቀር ዞሮ ዞሮ በሥልጣን ላይ ለመቆየትና ከሱም ጋር የተያያዙ መተኪያ የሌላቸውን የተግበሰበሱና በጣም የገዘፉ ጥቅሞች ማስጠበቁ እጅጉን አይሎ ስለሚገኝና የበለጠ ሚዛን-ደፊ ስለሚሆኑ፣ የድርጅቱን ቀደምት አቋሞች ቢያንስ እስካሁን ያለው አመራር እስካለ ድረስ አሁኑኑ ጨርሶ እርግፍ አድርገው መተው ባይቻለውም በሂደትና ቀስ-በቀስ "አዲሱ እምነት" ገዥነት እንዲኖረው ሁኔታው ያስገድዳል። ይኽ ደግሞ ኢሕአዴግ ወደ አንድ-ወጥ ድርጅትነት መቀየሩን የግድ ይላል። ይኽ ሂደት በምን ያኽል ፍጥነትና ደረጃ ሊከናወን መቻሉ ወይም ጠቀሜታውና ጉዳቱ በቅጡ ሊመረመር ይገባል።

ስለዚኽ ኢሕአዴግ መከተል ከተገደደበት በተቃርኖ የተወጠረ አካሄድና ከገባበት አጣብቂኝ ለመውጣት "የመንታ እናት" ሆኖ መቀጠል ስለማይቻለው የአንዱ ወይም የሌላው አዝማሚያ አይሎ እንዲወጣና በሌላው ላይ የማያሻማ ገዥነት ሊኖረው የሚችለው በአዎንታዊ ጎኑ አንድም ኢሕአዴግ አዲስ አመራር ሲኖረው አለያም ለአዎንታዊ ለውጥ የቆመው አገር-ወዳድና ሕዝባዊ ኃይል በአዲስ አገራዊ አስተሳሰብ ላይ የተመሠረተ አዲስ

አሠላለፍ ይዞ ቁርጠኛ ትግል ማድረግ ሲችል ብቻ ይሆናል፡፡ ለሁኔታው ወሳኝ መልስ የሚሆነው ግን በአብዛኛው በለውጥ ፈላጊው ወገን ጥንካሬ ላይ የወደቀ ነው፡፡

ስለሆነም በአገራችን አዎንታዊ ለውጥ እንዲመጣ የሚታገለው አገር-ወዳድና ሕዝባዊ ክፍል እራሱ የሚገኝበትን ሁኔታና ይኸ የኢሕአዴግ ውስጣዊ በተቃርኖ የተወጠረ ሽግሽግ ምን ያኸል በትግሉ መሣካት ላይ ጫና እንዳሳደረና ወደ-ፊትም ሊያሳድር እንደሚችል በቅጡ መገምገሙ አስፈላጊ ይሆናል፡፡ በአጭሩ ከዚኸ የአገዛዙ መሠረታዊ አቋሙን ያልለቀቀ ሆኖም አጠቃላይ የይዞታና የአሠላለፍ የሰመመ መሽጋሽግ አንፃር ለውጥ ፈላጊውን ክፍል ስናስተያይ በለውጥ ፈላጊው በኩል ያንን ያኸል መጣኝ የአስተሳሰብም ሆነ የአሠላለፍ መሽጋሽግ አልተደረገም ማለት ይቻላል፡፡ ቀጥሎ እስካሁን የተደረጉ የጋራ ጥረቶችን ስንመለከት እንደምንረዳው፣ ለውጥ ፈላጊው ወገን መሠረታዊ የአስተሳሰብ፣ የግብ-ትልምም ሆነ የስልት ይዞታው ላይ መጣኝ ለውጥ ሳያደርግ ኢሕአዴግ “የሽግግር መንግሥት” ከነበረበት ጊዜ አንስቶ በትግሉ የግብ ትልም (ስትራቴጂ) ሆነ በአደረጃጀት ይኸ ነው የሚባል ለውጥ በራሱ ላይ ሳያደርግ በአብላጫው አገዛዙን በመለወጥ ላይ ብቻ ያተኮረ ትግል እያደረገ መሆኑ ብዙ የሚያጠያይቅ ላይሆን ይችላል፡፡ ለአዎንታዊ ለውጥ ከቆመው ክፍል በአንዳንድ ወገኖች ዘንድ ይኸን ገዥ ክፍል የሚያዩት የዛሬ ሃያ ዓመት በሚያዩበት ዓይን እንጂ ከዚያ ወዲኸ ያለውን መሠረታዊ አቋሙን ያልለቀቀ ሆኖም አጠቃላይ የይዞታና የአሠላለፍ መሽጋሽግ ቁጥር ውስጥ ያላስገባ አካሄድ የሚያደርጉት ትግል መጣኝ የአሠላለፍና የስልት ለውጥ ሳያደርጉ እንዲቀጥሉ አድርጓቸዋል፡፡ በመሆኑም ለውጥ ፈላጊው ኃይል ቅድሚያን እየለቀቀና ተከላካይ እንዲሆን እራሱን እያመቻቸ፣ እራሱን እየበተነና እየሰነጠረ ጎራው እንዲሰበጣጠርና አቅሙ እንዲመነምን ሲያደርግ፣ አንድነቱም እንዲላላ ሲፈቅድ፤ በአንፃሩ ገዥው ክፍል ምንም እንኳ ከሕዝብ ጋር ያለውን ተቃርኖ በአብዛኛው እያከረረ መሄዱ አይቀሬ ቢሆንም ለጊዜው የበለጠ ሰብሰብ እያለና የውስጥ ድርጅታዊ አንድነቱንና ይዞታውን እንዲያጠናክር፣ የጥቅም ተጋሪዎችን ብዛት እንዲጨምርና አቅሙን ሊያጎለብት እንዲችል ሁኔታዎች እንዲፈቅዱለት መሆኑ እየታዬ ነው፡፡

ለአዎንታዊ ለውጥ የቆመው አገር-ወዳድና ሕዝባዊ ኃይል ከኢሕአዴግ ጋር ሊኖር የሚገባው ችግር ገዥው ክፍል ኢሕአዴግ ታሪክን ያልተመረኮዘ ፖለቲካዊ ብሔረሰበኝነት (ጎሠኝነት) ላይ የተመሠረተ ሕዝብን የሚከፋፍል የፖለቲካ ፍልሥፍናን ስለሚከተል፣ ለሁሉም ዜጎች እኩልነትን ለማስገኘት ድርጅታዊ ተፈጥሮው ስለማያስችለው፣ የሚከተለው አብዮታዊ ዴሞክራሲ የፖለቲካ ፍልሥፍና መድብለ-ፓርቲ ሥርዓትንም ሆነ የኤኮኖሚ እኩል ዕድልንና ተሣትፎን ስለማይፈቅድ፣ በነዚኸም ምክንያት ሰብኣዊ መብቶችን የሚጥስና በአጠቃላይ ኢ-ዴሞክራሲያዊ መሆኑ የግድ ስለሆነ፣ የአገርንና የሕዝብን ብሔራዊ ጥቅሞች የሚያስከብር ስላልሆነ፣ ወዘተ.. እንደሆነ የብዙዎች እምነት ነው፡፡ ይኸ ከሆነ በአገሪቱ ለውጥ እንዲመጣ የሚታገለው አገር-ወዳድና ሕዝባዊ (ዴሞክራት) ክፍል እስካሁን የሚከተለው የፖለቲካ ፍልሥፍና፣ አደረጃጀት፣ የትግል ስልትና የግብ ትልም (ስትራቴጂ) መጣኝ አይደለም፡፡ ስለሆነም እውነተኛ ለውጥን አያስገኝም፡፡

በአጠቃላይም ለለውጥ የቆመው ኃይል ኢሕአዴግ ትላንት ያደረገውን ብቻ ሣይሆን ትኩረቱ አሁን በሚያደርገውና በያዘው ትልም ከቀጠለ ደግሞ ነገ ሊያስከትል የሚችለውን አደጋ በቅጡ ገምግሞ በአሳማኝ መልኩ ማሣየትና ለዚያ ተአማኒነት ያለው አማራጭን ለሕዝብ ለማቅረብ አለመቻልን እንደሚያስከትል ሰብሰብ ባለ ሁኔታ ባለመጤኑ፣ ለአዎንታዊ ለውጥ የቆመው ኃይል “የጅል ዘፌ ሁሌ አባባዬ” ዓይነት በሚመስል ትብታቦ ተይዞ ብቁ ብሔራዊ አማራጭ የመሆን አቅሙን እያኮሰሰ መሄዱ በቁጭት የሚታይ ሆኖ መቀጠል የማይኖርበትና ይቅርታ የሌለው ድክመት በመሆኑ መርኅን የተከተለ ጠንካራ ምላሽን በአስቸኳይ ይጠይቃል፡፡ ለዚኸም ነው የመጀመሪያው ጥረት ያለፉ የጋራ ትግል ልምዶችን በቅርበት መመርመሩ አስፈላጊ የሚሆነው፡፡

ሐ - ፩፡- የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ቅንጅት (ኢዴኃቅ)

***በክፍል አምስት ይቀጥላል ……***